# የኢሰመኮ 4ኛ ዙር የሰብአዊ መብቶች ፊልም ፌስቲቫል የፎቶግራፍ፣ የሥዕልእና የአጫጭር ሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ውድድር

## አጠቃላይ የውድድር መርሖች እና ደንቦች

በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) አዘጋጅነት የሚካሄደው ዓመታዊው የሰብአዊ መብቶች ፊልም ፌስቲቫል ዋነኛ ዓላማ (December 10) የሚውለውን ዓለም አቀፉን የሰብአዊ መብቶች ቀን ለማሰብ፣ የኪነጥበብን እና የሰብአዊ መብቶችን ትስስር ለማጠናከር፣ በሁለቱ ዘርፎች መካከል ያለውን ጥምረት በተመለከተ ግንዛቤ ለማስፋፋት፣ እንዲሁም ኪነጥበብ ***"ሰብአዊ መብቶች ባህል የሆኑባት ኢትዮጵያን ማየት"*** የሚለውን የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ራዕይ ለማሳካት ያለውን ከፍተኛ አስተዋጽዖ ለማስታወስ ነው:: በተጨማሪም የፊልም ፌስቲቫሉ የኪነጥበብ ሥራዎችን በውድድር መልኩ በማሳተፍ፣ በየዓመቱ በሚያሳትፋቸው የኪነጥበብ ዘርፎች፣ በጥራቱ፣ ዝግጅቱ በሚካሄድባቸው አካባቢዎች እና ቦታዎች፣ በታዳሚዎች ብዛት እና ለሰብአዊ መብቶች በሚያደርጉት አስተዋጽዖ ብዝኃነት፣ በሚያካትታቸው የቋንቋዎች እና የማኅበረሰብ ክፍሎች ብዝኃነት እና በመሳሰሉት መስፈርቶች ሁሉ በየጊዜው እድገት በማሳየት፣ በውድድር ለሚሳተፉ የኪነጥበብ ባለሞያዎችም ሆነ በሰብአዊ መብቶች ዘርፎች ለሚሠሩ ለሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ተቋማት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መድረክ ለመሆን ያለመ ነው::

በመሆኑም ኢሰመኮ በሁሉም የሥራ ዘርፎቹ ተግባራዊ የሚያደርጋቸው እሴቶች እና መርሖች በሁሉም የፊልም ፌስቲቫል ዝግጅት ሂደቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ:: ኢሰመኮ የተቋቋመበትን ዓላማ እና ተልዕኮ ለማሳካት የሚከተሉትን እሴቶች እና መርሖችን በመከተል ይሠራል፦

- *ለእኩልነት፣ ለሰብአዊ ክብር እና ለፍትሕ ባለን ቁርጠኝነት ላይ በመመሥረት የኢሰመኮ እሴቶች የሚከተሉት ናቸው፦ ገለልተኝነት፣ አካታችነት፣ ለጉዳት ተጋላጭ ከሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጎን መቆም፣ እውነተኝነት እና በመልካም ሥነ ምግባር መመራት፣*

- *በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት፣ ሀገሪቱ ተቀብላ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ስምምነቶች ዕውቅና ባገኙ ሰብአዊ መብቶች መሠረት እና በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ድንጋጌዎች እና መርሖችን መሠረት በማድረግ መሥራት፣*

- *በአፍሪካ የሰዎች እና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን የወጣው እና ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት እና በሰብአዊ መብቶች ዘርፍ ለሚሠሩ ተቋማት የአጋር ተቋም ደረጃን ለመስጠት የአቋም መግለጫ (ACHPR/Res.370(LX)2017)፣ እንዲሁም ዓለም አቀፍ የብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት የሚመለከቱ መርሖች (የፓሪስ መርሖች) ማዕቀፍ መሠረት መሥራት::*

ይህንን መሠረት በማድረግ፦

1. ኢሰመኮ ከላይ የተዘረዘሩትን መርሖች እና በዚህ ቅጽ የተዘረዘሩ ደንቦች የሚተላለፉ፣ በማናቸውም ሁኔታ የሰብአዊ መብቶችን መርሖች እና ድንጋጌዎች የማያከብሩ ወይም ከሰብአዊ መብቶች መርሖች እና ድንጋጌዎች ጋር የማይጣጣሙ የተሳታፊዎች የኪነ ጥበብ ሥራዎችን ያለማካተት፣ ከውድድር ውጪ እንዲሆኑ የማድረግ ወይም ወደ ሌላ ዙር እንዳይሸጋገሩ የማድረግ ሙሉ መብቱ የተጠበቀ ነው:: ይህ የኢሰመኮ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል::

2. በዚህ ውድድር በመሳተፍ እና የኪነጥበብ ሥራ ለውድድር ለማቅረብ በመስማማት፣ ኢሰመኮ ከሰዎች የግል መረጃ እና የግል ሕይወት (privacy) መብት ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎችን እና መርሖችን ባከበረ መልኩ፣ በዚህ ቅጽ እና በኪነጥበብ ሥራው የተካተቱ መረጃዎች እንደ አግባብነቱ እና ለትርፍ ላልሆነ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ተሳታፊዎች ይስማማሉ። መሠረታዊ የፈጠራ ሥራዎች የጋራ መመሪያዎች እና ደንቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ (Creative Commons Rules Apply)።

3. ተሳታፊዎች በማንኛውም ዘርፍ ለውድድር የሚያቀርቧቸው የኪነጥበብ ሥራዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ደንቦች ሊያከብሩ ይገባል፦

   ሀ. ለውድድር የቀረበው የኪነጥበብ ሥራ ባለሙሉ መብት ባለቤት መሆን እና ለውድድር የቀረበውን የኪነጥበብ ሥራ ለውድድር ለማቅረብ መብት ያለው መሆን፣

   ለ. ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ተሳታፊዎች የተሳትፎ ቅጹን በአንድ አሳዳጊ ወይም በሕግ መብት የተሰጠው አሳዳጊ፣ ወላጅ ወይም ሞግዚት እንዲያስፈርሙ ይጠበቃል። ይህንን መስፈርት ያላሟሉ እና ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ተሳታፊዎች የኪነጥበብ ሥራዎች ከውድድር ውጪ ይሆናሉ።

   ሐ. ለውድድር የቀረበው የኪነጥበብ ሥራ በውስጡ ሰዎችን ወይም ተቋማትን (የሦስተኛ ወገን) ወይም ተሳታፊውን ለመለየት እና ለማንኛውም ዐይነት ሥጋት የሚያጋልጥ የግል መረጃ እንደማያካትት ማረጋገጥ፣ (ለምሳሌ ሙሉ ስም እና የመኖሪያ አድራሻ)

   መ. ለውድድር የቀረበው የኪነጥበብ ሥራ የሀገሪቱን ሕግጋት እና ድንጋጌዎች፣ እንዲሁም የሰብአዊ መብቶችን መርሖች እና ድንጋጌዎች የማይተላለፍ እና የማይጥስ፣ ሦስተኛ ወገኖችን (ሌሎች ሰዎችን ወይም ተቋማትን) የማያስፈራራ፣ ሐሰተኛ ወይም አሳሳች የሆነ መረጃ፣ ሰዎችን ወይም ተቋማትን (ሦስተኛ ወገኖችን) የማይዘልፍ/የማያንገላታ፣ የሰዎችን ወይም ተቋማትን (ሦስተኛ ወገኖችን) መልካም ስም እና ዝና የማያጠፋ፣ በሦስተኛ ወገን የማያስከስስ፣ ሃይማኖታዊ፣ የብሔር ወይም የፖለቲካ አጀንዳ የማያራምድ፣ ወሲባዊ ይዘት የሌለው ወይም በማናቸውም መልኩ ለአደጋ እና ሥጋት የማያነሳሳ መሆኑን ማረጋገጥ፣

   ሠ. ለውድድር የቀረበው የኪነጥበብ ሥራ የሦስተኛ ወገኖችን (ተቋማት ወይም ሰዎች) የባለቤትነት/የፈጠራ መብት (ኮፒራይት)፣ የንግድ ሥራ ምልክት፣ አርማ፣ እንዲሁም የግል መረጃ እና ማስታወቂያን የተመለከቱ ሕግጋትን እና ደንቦችን ጨምሮ ማናቸውንም ዐይነት የሥነ አእምሮ ውጤቶች መብቶችን የማይተላለፍ/የማይጥስ መሆኑን ማረጋገጥ፣

   ረ. በተራ ቁጥር 3 (ሠ) የተዘረዘረው የሰዎችንም ሆነ የተቋማትን ስሞች ወይም ለመለየት በማያስችል መልኩ የተቀራረቡ መረጃዎችን፣ የሰዎችን ወይም የተቋማትን ድምጽ እና ተያያዥ መረጃዎችን ወይም ውጤቶችን ጨምሮ ሌሎች በሕዝብ የሚታወቁ በሕይወት ያሉም ሆነ በሕይወት የሌሉ ሰዎችን እና ሥራዎቻቸው ጋር የሚመሳሰሉ ሥራዎችን የሚጨምር ነው፣

ሰ. የንግድ ወይም የማስተዋወቅ ዓላማ ያላቸው እና አንድን ምርት ወይም አገልግሎት የሚያስተዋውቁ ይዘት ያላቸው የኪነጥበብ ሥራዎች አለመሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ሸ. የኪነጥበብ ሥራውን በመሥራት ሂደት ማንኛውም ሰው ላይ ጉዳት አለመድረሱን፣ ማንኛውም ዐይነት እንስሳ/እንስሳት ላይ የምርምር እና የጭካኔ ተግባር የመሳሰሉ ጉዳዮች አለመድረሱን ማረጋገጥ፣

4. በእነዚህ ደንቦች መተላለፍ ሳቢያ በኢሰመኮ ላይ የሚደርሱ ማናቸውንም የካሳ፣ የክፍያ ወይም ሌሎች ገንዘብ ነክ ወጪዎችን ኃላፊነት መውሰድ፣

5. ለውድድር በቀረበው የኪነጥበብ ሥራ የሚታዩ ማናቸውንም ሰዎች እና ተቋማት ሙሉ ፈቃድ መኖሩን ማረጋገጥ ይገባል:: ይህም ለሥራው ያገለገሉ እና በኪራይ ወይም በውሰት የተገኙ ማናቸውንም አልባሳት፣ ተጨማሪ ግብዓቶችንም ያካትታል::

6. በኪነጥበብ ሥራዎች ግምገማ፣ እጩ መረጣ ወይም የአሸናፊዎች መረጣ እና ተያያዥ ሂደት ወቅት ማናቸውም ዐይነት የሥነ-ምግባር ጉድለቶች ወይም የሕግ መተላለፎች መኖራቸው የተረጋገጠ ከሆነ ኢሰመኮ ይህን መተላለፍ በፈጸሙ ተሳታፊዎች የቀረቡ የኪነጥበብ ሥራዎችን ከውድድሩ ውጪ የማድረግ፣ ወይም ውድድሩን የመሰረዝ ወይም የእጩዎችን ዝርዝር ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ እና ሽልማቶችን የመሰረዝ እና ተያያዥ የእርምት ውሳኔዎችን የመውሰድ ሙሉ መብት አለው:: ይህ የኢሰመኮ ውሳኔ የመጨረሻ ነው::

7. በተራ ቁጥር (2) የተገለጸው ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢሰመኮ ለውድድሩ የቀረቡ የኪነጥበብ ሥራዎችን ሙሉ ባለቤትነት እና ይህንን የሚያሳይ ዕውቅና ይሰጣል::

8. በዚህ ደንብ ተራ ቁጥር (2) የተገለጸው ለትርፍ ወይም ለንግድ የማይውሉ ጥቅሞች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትንም ያካትታል::

ሀ. በውድድሩ ግምገማ ሂደቶች በሙሉ እና ለዝግጅቱ አስፈላጊ የሆኑ የማስተዋወቂያ ሥራዎች፣

ለ. በዝግጅቱ ለሚቀርቡ እና ከዝግጅቱ በኋላ አስፈላጊ ለሆኑ ዐውደ ርዕዮች ወይም የኢሰመኮ ሌሎች ዝግጅቶች፣ መድረኮች፣ ማስተዋወቂያ ሥራዎች፣

ሐ. በኢሰመኮ ድረገጽ እና ማኅበራዊ ሚድያ ገጾች፣ ሌሎች መገናኛ ብዙኃን ወይም የስርጭት መንገዶች፣ እንዲሁም

መ. ከዚሁ ጋር የተያያዙ እና ለመገናኛ ብዙኃን ወይም ለኢሰመኮ አጋር ድርጅቶች የሚሰራጩ የማስተማሪያ፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ፣ የትምህርት፣ የውትወታ፣ የሪፖርት እና ተያያዥ ሌሎች ተግባራት እና ሥራዎች::

9. ኢሰመኮ ለውድድር የቀረቡ የኪነጥበብ ሥራዎችን ያለ ተሳታፊው/ባለቤቱ ፈቃድ ለሽያጭ ወይም በተራ ቁጥር (2) የተዘረዘረውን የመጠቀም መብት ለንግድ/ለትርፍ ለሚያውሉ ሦስተኛ ወገኖች አያስተላልፍም::

10. ኢሰመኮ ለውድድር የቀረቡ የኪነጥበብ ሥራዎችን በተራ ቁጥር (2) እና በተራ ቁጥር (8) በተገለጸው መልኩ ጥቅም ላይ በሚያውልበት ወቅት የኪነጥበብ ሥራውን ባለቤትነት (Credit Line) ይገልጻል:: የኪነጥበብ ሥራው ባለቤት ይህ አለመደረጉን

ለኢሰመኮ ባሳወቀ በ21 የሥራ ቀናት ውስጥ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡ [1]

11. በማናቸውም ዘርፍ በውድድሩ የሚሳተፉ ሰዎች እና ተቋማት ለውድድሩ፣ ለፊልም ፌስቲቫሉ ወይም ተያያዥ የሆኑ የኢሰመኮ ዝግጅት ማስተዋወቂያ ለሚሆኑ ካታሎጎች፣ ጽሑፎች ወይም ሌሎች ስርጭቶች ስማቸው እና ፎቶግራፋቸው (ምስላቸው) ያለተጨማሪ ክፍያ እንዲገለጽ እና በእነዚህ ሥራዎች ለመሳተፍ ይስማማሉ፣ ተገቢውን ትብብርም ያደርጋሉ፡፡

---

[1] The Ethiopian Human Rights Commission (EHRC) assumes no responsibility for any incorrect, inaccurate or incomplete information, whether caused by website users or by any of the equipment or programming associated with or utilized in the Competition, and the Ethiopian Human Rights Commission (EHRC) assumes no responsibility for technical, hardware or software failures of any kind, for lost network connections, garbled computer transmissions, other problems or technical malfunctions with regard to the Competition. The Ethiopian Human Rights Commission (EHRC) assumes no responsibility for any error, omission, corruption, interruption, deletion, defect, delay in operation or transmission, communications line failure, theft or destruction or unauthorized access to or alteration of Entries. The Ethiopian Human Rights Commission (EHRC) is not responsible for any problems or technical malfunction of any telephone network or lines, computer on-line systems, servers, computer equipment, software, failure of any e-mail addressed to the Ethiopian Human Rights Commission (EHRC) on account of technical problems, human error or traffic congestion on the internet or any website, or any combination thereof, including any injury or damage to Your or any other person's computer related to or resulting from participation or downloading any materials in the Competition. If for any reason a contestant's entry cannot be viewed or is not capable of running as planned, including infection by computer viruses, bugs, tampering, unauthorized intervention, fraud or technical failures, the Ethiopian Human Rights Commission (EHRC) assumes no responsibility.

In no event will the Ethiopian Human Rights Commission (EHRC), its partners and related organizations, Event Partners, its advertising or promotion agencies, or its Commissioners, Directors, Employees, representatives or agents be responsible or liable for any damages or losses of any kind, including direct, indirect, incidental, consequential, special or punitive damages arising out of any Entrant's access to and use of the Website. Without limiting the generality of the foregoing, everything on the Website is provided "as is" without warranty of any kind, either expressed or implied, including but not limited to, the implied warranty of merchantability, fitness for purpose or use or non-infringement.